# ደንብ

ሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS)

ተዛማጅ ሠነዶች፡- GEARB, IJA, IJARA

ኃላፊነት ያለው ቢሮ፡- Deputy Superintendent of Schoolsየት/ቤቶች ምክትል ሱፐርኢንተንደንት

## Early Entrance to Prekindergarten, Kindergarten, and First Grade
## ወደ ቅድመ መዋዕለ ህጻናት፣ መዋዕለ ህጻናት እና አንደኛ ክፍል ቀድመው ለሚገቡ

I. ዓላማ

ወደ ቅድመ መዋዕለ ህጻናት፣ መዋለ ህፃናት እና አንደኛ ክፍል መግቢያን በተመለከተ መመሪያዎችን ለመደንገግ

II. ዳራ

የሜሪላንድ ስቴት ደንብ ለቅድመ መዋዕለ ሕጻናት፣ መዋለ ሕጻናት እና አንደኛ ክፍል የመግቢያ ዕድሜን ይደነግጋል። እነዚህ ዕድሜዎች ለዚህ ደንብ ዓላማዎች ተገቢ ናቸው ተብሎ ይታሰባል።የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ቦርድ ወደ መዋእለ ህጻናት የሚገቡትን ህፃናት እድሜ ቀስ በቀስ የሚጨምር የመግቢያ ቀናትን አጽድቋል። የመዋዕለ ሕፃናት የመግቢያ ቀናት ቀስ በቀስ የሚጨምረው 2003-2004 የትምህርት ዓመት ነው። በተጨማሪም፣ ቀደም ብሎ ለመቀበል የሚያስችል ከአቻ ቡድን ከሚጠበቀው በላይ ችሎታዎችን የሚያሳይ/የምታሳይ መሆኑ ከተረጋገጠ በሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ዲፓርትመንት ደንብ (JEBEA) መሠረት የአካባቢው ሱፐርኢንተንደንት ወይም ተወካይ ከወሰነ(ች) በወላጅ ጥያቄ በመመሥረት፤ በአካባቢ የትምህርት ቦርድ ደንብ አምስት አመት የሆናቸውን ህጻናት ወደ አንደኛ ክፍል እንዲገቡ ይደነገጋል።

III. መመሪያዎች/ሒደት/አካሄድ

A. የመዋለ ሕጻናት መግቢያ ዕድሜ

1. ወደ ቅድመ መዋለ ህፃናት የሚገባ/የምትገባ ተማሪ ተማሪው(ዋ) ለመግቢያ ባመለከተ(ች)በት የትምህርት አመት ሴፕቴምበር 1 አራት አመት እድሜ ወይም ከዚያ በላይ መሆን አለበት።

2. በስቴት ደንብ መሠረት የገቢ-ብቃት ላላቸው ቤተሰቦች ቅድመ ምዋእለ ህፃናት ይገኛል። ወደ ቅድመ መዋለ ሕጻናት ቀደም ብለው ለመግባት የሚፈልጉ ሁሉ በመዋዕለ ሕፃናት ውስጥ ትምህርት የመቀበል ስኬት ላይ ተፅእኖ የሚያሳድር ስለሚሆን ቀደም ብለው ወደ ትምህርት የመግባት ፍላጎት እንዳላቸው በተረጋገጠ ሁኔታ ማሳየት አለባቸው።

   a. የቅድመ መዋዕለ ሕፃናት ማመልከቻ ቅጾች ከህጻናት ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች ክፍል/Division of Early Childhood Programs and Services ይገኛሉ። እነዚህ ቅጾች እንዳሉ ለወላጆች ይነገራቸዋል። የተሟሉ የማመልከቻ ቅጾችን ከፌብሩወሪ 1 እስከ ጁን 30 ማቅረብ ይቻላል።

b. የስቴት ነፃ እና የቅናሽ ዋጋ የምግብ ስርዓት (FARMS) መመሪያዎችን የሚያሟላ የቤተሰብን የገቢ መጠን ማረጋገጫ ሰነድ ያስፈልጋል።

c. የእድገት ሁኔታዎች ላይ ተፅእኖ የሚያደርግ ቢሆንም ቅድመ ትምህርትን የሚደግፉና የሚያረጋግጡ ተጨማሪ ሰነዶች ሊቀርቡ ይችላሉ።

d. ልጁ/ልጅቱ በቅድሚያ መዋእለ ህጻናት የመግባት ሂደትን ተከትሎ የገባ(ች) ካልሆነ በስተቀር፥ ቀደም ብሎ ወደ ቅድመ መዋዕለ ሕፃናት መግባት የሁለት ዓመት የቅድመ መዋዕለ ሕፃናት ትምህርትን ያስከትላል።

3. የቅድመ መዋዕለ ሕፃናት መግቢያ ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች ክፍል (The Division of Early Childhood Programs and Services) ወደ ቅድመ መዋእለ ህጻናት በቅድሚያ የመግባት ሂደትን የማጣራትና የማስተዳደር ኃላፊነት አለበት።

B. ወደ መዋእለ ህጻናት መግቢያ እድሜ

1. 2006–2007 የትምህርት ዘመን ጀምሮ፣ ተማሪዎች ወደ መዋእለ ህጻናት ለመግባት ብቁ ለመሆን ሴፕቴምበር 1 ላይ 5 አመት መሆን አለባቸው።

2. የልደታቸው ቀን በስድስት ሳምንት ጊዜ ውስጥ ከስቴቱ የመግቢያ ቀን ድንጋጌ በላይ የሆነ፣ ወደ መዋለ ህፃናት ቀደም ብለው ለማስገባት የሚፈልጉ ወላጆች፣ የልጃቸውን የምዝገባ ማመልከቻ ለመደገፍ የሚከተሉትን ሰነዶች ማቅረብ አለባቸው።

a. MCPS Form 271-6 (ገጽ 1)፡ ወደ መዋእለ ህጻናት/ኪንደርጋርተን ፕሮግራም ቀደም ብሎ የመግባት ማመልከቻ። እነዚህ ቅጾች እንዳሉ ለወላጆች ይነገራቸዋል።

b. MCPS Form 271-6 (ገጽ 2)፡ ወደ መዋእለ ህጻናት/ኪንደርጋርተን ቀደም ብሎ የመግባት ማመልከቻ፡- የሜሪላንድ ለትምህርት ቤት ዝግጁነት ሞዴል (MMSR) ተለይተው የታወቁ አመላካች ችሎታዎች የወላጅ ማረጋገጫ ዝርዝር።

c. በችሎታ ምዘና ቀን ተማሪው(ዋ) ደህና መሆኑ(ኗ)ን እና መገምገም የሚቻል መሆኑን የወላጅ ማረጋገጫ።

3. በተጨማሪም፣ ወላጆች ከሚከተሉት አማራጮች ውስጥ የሚፈልጉትን የማመልከቻው አካል አድርገው ማስገባት ይችላሉ።

a. የቅድመ ትምህርት ቤት ክትትል ሪፖርቶች፣ ሪከርዶች እና ግምገማዎች አካዴሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ስሜታዊ እና አካላዊ ብስለት፣ የአንጎል አስተሳሰብ እድገት፣ የመማር ችሎታዎች እና ወደ ት/ቤት ቀደም ብሎ መግባትን የሚመለከቱ ሰነዶች
b. በውጭ ባለሙያዎች የተጠናቀቀ መደበኛ የተማሪ ችሎታ ግምገማዎች

4. ወደ መዋእለ ህጻናት/ኪንደርጋርተን ቀደም ብሎ ለማስገባት ማመልከቻዎችን ከፌብሩዋሪ 1 እስከ ጁን 30 ድረስ ብቻ ማቅረብ ይቻላል።

5. የማጣራት ሂደት

   a. ቀዳሚ የልጅነት ፕሮግራሞች እና አገልግሎቶች ክፍል ከርዕሰ መምህራን ጋር በመተባበር ወደ መዋእለ ህጻናት/ኪንደርጋርተን ቀደም ብሎ ለመግባት የማጣራት ሂደቱን የመምራትና የማስተዳደር ሃላፊነት አለበት።

   b. የማጣራት ሂደቶቹ አካዴሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ስሜታዊ እና አካላዊ ብስለት፣ የአንጎል እድገት፣ የመማር ችሎታ እና ቀደም ብሎ ወደ ት/ቤት መግባት እንደሚችል/እንደምትችል የሚያረጋግጡ ችሎታዎችን ለመገምገም ይጠቅማሉ። ለማጣሪያ ሂደቱ ጥቅም ላይ የሚውሉ ደረጃቸውን የጠበቁ መሳሪያ(ዎች)፣ ችሎታን በታዛቢነት ማጤን እና በሰራተኞች የሚጠናቀቁ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የመጀመሪያ ደረጃ ግምገማዎች እና ከወላጆች የተገኙ መረጃዎችን ያካትታሉ።

   c. የማጣሪያ መተግበሪያዎቹ የሚከተሉትን ማካተት አለባቸው፡-
      የንባብ/የቋንቋ ስነጥበብ ግምገማ
      የሒሳብ መመዘኛ
      የአካል ደህንነት እና የአንጎል እድገት፣ ግላዊ እና የማህበራዊ ስሜት እድገት፣ ቋንቋ እና ስነ-ጽሁፍ እና የሂሳብ አስተሳሰብን ጨምሮ MMSR አመላካች ችሎታ ጋር የተጣጣመ የእይታ ግምገማ

6. ከሁለተኛው ሳምንት የትምህርት ማብቂያ ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ፣ ልጆቻቸውን በቅድመ ት/ቤት መግቢያ ሂደት ያስገቡ ወላጆች ከተማሪው(ዋ) እና ቤተሰብ በክፍል ደረጃ የሚጠበቁትን ሁኔታዎች ለመገምገም ከትምህርት ቤቱ ጋር በቅድመ መግቢያ ኮንፈረንስ ላይ መሳተፍ ይጠበቅባቸዋል።

C. ወደ አንደኛ ክፍል መግቢያ ዕድሜ

2007-2008 የትምህርት ዘመን ጀምሮ፣ ተማሪዎች ሴፕቴምበር 1 ላይ 6 አመት መሆን አለባቸው። የተወለዱበት ቀን ከስቴቱ የመግቢያ ቀን በስድስት ሳምንት ጊዜ ውስጥ የሚሞላቸው ልጆች ወደ አንደኛ ክፍል ቀድመው ለመግባት ሊፈቀድላቸው ይችላል።

1. ቀደም ብሎ ወደ አንደኛ ክፍል የመግባት ብቃት
   አንድ ተማሪ ቀደም ብሎ ወደ አንደኛ ክፍል ለመግባት የሚችለው/የምትችለው፡-

   a. ተማሪው(ዋ) በተለያዩ የትምህርት ዘርፎች ከአማካይ ውጤት በላይ አፈጻጸም እና እድገትን የሚያሳዩ የማህበራዊ-ስሜታዊ ክህሎቶችን እና የአካዳሚክ ክህሎቶችን ማሳየት አለበ(ባ)ት። እንደዚህ አይነት ችሎታዎች ምደባ በተጠየቀበት የክፍል ደረጃ የሚጠበቁትን ማሟላት ወይም ማለፍ አለባቸው

   b. ተማሪው(ዋ) ለ1ኛ ክፍል ተስማሚ በሆኑ ማህበራዊ፣ ስሜታዊ እና አካላዊ ብስለት፣ የአንጎል እድገት እና የመማር ችሎታዎችን ማሳየት አለበት።

   c. ወላጅ/አሳዳጊ ልጃቸውን ለማስገባት በጽሁፍ መጠየቅ አለባቸው

2. ማመልከቻ

a. ቅጽ 271l፣ ወደ አንደኛ ክፍል ቀደም ብሎ የመግባት ማመልከቻ፣ በሁሉም አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚገኝ ሲሆን ወላጆች ከጠየቁ ይሰጣል። እንዲሁም MCPS ድረ-ገጽ ላይ ይገኛል። እነዚህ ቅጾች እንዳሉ ለወላጆች ይነገራቸዋል።

b. ልጁ/ልጅቱ ከስድስት ሳምንት ላልበለጠ ጊዜ ወደ መዋእለ ህጻናት/ኪንደርጋርተን እንዲገባ ይጠበቅበ(ባ)ታል፥ ከዚያም ወደ አንደኛ ክፍል ቀደም ብሎ ለመግባት እንደ እጩ ሊሆን ይችላል/ዕጩ ልትሆን ትችላለች።

c. ከወላጆች የሚቀርቡት ማመልከቻዎች ከጁላይ 1 ጀምሮ የትምህርት ቤት የመጀመሪያ ሳምንት አርብ መካከል መቅረብ አለባቸው።

d. የአንደኛ ክፍል ምደባን በተመለከተ ሁሉም ውሳኔዎች ከኦክቶበር 15 በፊት ይከናወናሉ።

3. የማጣራት ሒደት

a. ርእሰ መምህሩ(ሯ) ቀደም ብሎ ወደ አንደኛ ክፍል ለመግባት የማጣራት ሂደቱን የመምራትና የማስተዳደር ሃላፊነት አለበ(ባ)ት።

b. የማጣራት ሂደቶቹ አካዴሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ስሜታዊ እና አካላዊ ብስለት፣ የአንጎል እድገት እና የመማር ችሎታን ለመገምገም ጥቅም ላይ ይውላሉ። ጥቅም ላይ የሚውሉት የማጣራት ሂደቶች ደረጃውን የጠበቀ መሳሪያ(ዎች)/ኢንስትሩሜንትስ፣ እንቅስቃሴዎችን መታዘብ እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የመጀመሪያ ደረጃ የሰራተኞች ግምገማዎች እና የወላጆች መረጃዎችን ያካትታሉ።

c. የማጣራት መገልገያዎች የሚያካትቱት:-
የንባብ/የቋንቋ ስነጥበብ ግምገማ
የሒሳብ መመዘኛ
ማህበራዊ፣ ስሜታዊ እና አካላዊ እድገትን ጨምሮ የእድገት ሁኔታዎች ምልከታና ግምገማ

4. ግምገማ እና ምደባ

a. ርእሰ መምህሩ የማጣሪያ መረጃውን እና በወላጆች የቀረቡ ሌሎች ተዛማጅ ሰነዶችን በትምህርት አስተዳደር ቡድን (EMT) ወይም የትብብር እርምጃ ሂደት (CAP) ለመገምገም ቀጠሮ ያስይዛል/ታስይዛለች።

b. በማንኛውም የአንድ አይነት መሳሪያ ግምገማ ላይ ብቻ በመመስረት ምንም አይነት ውሳኔ አይደረግም።

c. ምደባን በተመለከተ EMT ውሳኔ ይሰጣል፣ እና ርእሰመምህሩ ወይም "Division of Early Childhood Programs and Services" እንደአግባቡ፣ ማጣሪያው በተደረገ 15 ቀናት ውስጥ ለወላጅ በጽሁፍ ያሳውቃል።

D. ይግባኝ የመጠየቅ ሒደት

ወላጅ MCPS Regulation KLARAከህዝብ ለሚመጡ ጥያቄዎች እና ቅሬታዎች ምላሽ መስጠት ደንብ መሠረት በቅድመ መግቢያ ውሳኔዎች ላይ ቅሬታ ካላቸው ይግባኝ ማለት ይችላሉ።

ስለ ደንቡ ታሪክ፦ አዲስ ደንብ፣ ጁን 1983 እና ሜይ 2, 2006 ክለሳ ተደርጓል።